7 ኛ ክፍል ስነ-ዜጋ

ምዕራፍ ዘጠን

ርዕስ የቁጠባ ባህል

9.1 የቁጠባ ዓይነቶች

የቁጠባ ባህል ማዳበር የተረጋጋ እና ሰላማዊ ሂወት ለመምራት ያስችላል ስለ ቁጠባ ጥሩ ግንዛቤ ያለው ግንዛቤ ከሌለው በእጅጉ የተሻለ ነው።

የቁጠባ ዓይነቶች የምንላቸው፡-

1. የዓይነት ቁጠባ
2. የገንዘብ ቁጠባ
3. የጊዜ ቁጠባ

1. የዓይነት የሚደረግ ቁጠባ በገንዘብ ሳይሆን ቋሚ በሆኑ ንብረቶች የሚገለፅ ነው። ለምሳሌ ውድ እቃዎችና እና የከበሩ ድንጋዮቸን ገዝቶ በማስቀምጀ እንስሳትን በማርባት ቋሚ ተክሎችን በመትከል ቤት መስራት የመሳሰሉት ናቸው።

   በዓይነት የሚደረጉ የቁጠባ ዘዴዎችን በማንኛውም የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ ሰዎች ሊከተሉ የሚገባ ነው። <u>ለምሳሌ</u> በገጠር በአንድ ቦታዎች የሚኖሩ ቤተሰቦች እንስሳትን ተንከባክበው ማሳደግ፣ ቋሚ ተክል መትከል ቡና፣ዛፍ

2. የገንዘብ ቁጠባ፡- የገንዘብ ቁጠበባ የሚባለው በገንዘብ የሚደረግ ቁጠባ ነው። በአሁኑ ጊዜ የተለያዩ አገልግሎቶች እና ልውውጥ የሚደረገው በገንዘብ ነው በገንዘብ ቁጣባ ወቅት ለእለታዊ ነገሮች የሚያስፈልጉንን ካደረግን በኋላ ለነገ ሂወታችን የሚጠቅመንን ማስቀመጥ እንችላል። የገንዘብ ቁጠባ ለማድረግ ባንክ ተመራጭ እና አስተማማኝ ነው። ስለዚህ ካለ ስጋት ገንዘባችንን ማስቀመጥ እንችላለን ባንክ በፈለግነው ጊዜ አስቀምጠን በፈለግነው ጊዜ አውጥተን መጠቀም እንችላለን።

3. የጊዜ ቁጠባ በሰዎች የዕለት ከእለት ህይወት ውስጥ ጊዜ ትልቅ ሚና አለው የጊዜን አጠቃቀም የማወቅና ያልተረዳ ሰው አስቀድሞ እጁን ለድህነት ይሰጣል። የወደፊት ሂወቱም አንድም ተስፋ ሰጪ አይሆንም። የጊዜ ቁጠባ የምንለው በአጭር ሰዓት ውስጥ ብዙ ስራ መስራትና ውጤታማ ስራ ማከናወን ነው። ለጠንካራ የሥራ ባህል መዳበር የጊዜን ጥቅም ማወቅ ከፍተኛ ሚና አለው። የጊዜ ሰሌዳ አጠቃቀም ለጊዜ ቁጠባ የራሱ የሆነ አስተዋፅኦ አለው። ስለ ገንዘብ የተባሉ አባባሎች በምሳሌነት እንመልከት

ገንዘብን የተመለከተ

- ❖ ገንዘብ ካለ በሰማይ መንገድ አለ
- ❖ ወርቅ የተጫነች አህያ በሮች ይከፈቱላታል

ጊዜን የተመለከተ አባባል

- ❖ ጊዜ ወርቅ ነው!
- ❖ ጊዜ ቆሞ አይጠብቅም ታክሲ አይደለም

9.2 <u>የቁጠባ ባህል</u>

‹‹በበጋ ፀሀይ ፈራ በክረምት ዝናብ ፈራ ልጂ እንጀራ ቢለው በጅብ አስፈራራ›› አብዛኛውን የኢትዮጵያ ህዝቦች ኑሮ የተመሰረተው በቤተሰብ እርስ በርስ መደጋገፍ ላይ ነው። የቁጠባ ባህል ማላት የተቆጠበን ንብረት ወይም ገንዘብ በአንድ ጊዜ ማውደም አይደለም።

ቁጠባ ሁለት መሰረታዊ ምክንያቶች አላት፡-

1. ለሚጠበቁና ለማይጠበቁ አጋጣሚዎች ወይም ችግሮች ለማዋል ለሚጠበቁ ስንል፡- ልደት የመስቀል በዓል፣ አረፋ መውሊድ የቤት ከራይ የመሳሰሉት ናቸው

   <u>የማይጠበቁ</u>፡- አደጋ፤ ህመም፤ሞት የመሳሰሉት ናቸው።

ቋሚ ንብረት ለማፍራት ሰዎች በተረጋጋ ኑሮ ውስጥ ካሉ ለረዥም ጊዜ የሚገለገሉባቸውን ከዚያም ከራሳቸው አልፈው ለቀጣይ ትውልድ የሚሸጋገሩ ንብረቶችን ያፈራሉ። ለምሳሌ ቤት መስራት ቡና እና እንሰት መትከል ደን ማልማት የቤት እንስሳት ማራባት።

9.3 በእቅድ መመራት

እቅድ አንድን ስራ ለመስራት ወይም ውጤት ለማግኘት የምንጠቀምበት የአሰራር ስልት መንደፍ ማለት ነው። ያንን የዐሰራር ዓይነት በጊዜ ለአተገባብ የሚጠቅሙ ስልቶችን መቀየስ ነው።

እቅድን ለማስፈጸም የሚረዱ ስልቶች ይኖራሉ። ለምሳሌ ገንዘብ በሚመለከት እቁብ መጣል። ወይም ከመጀመሪያ ከሚገኝ ገቢ ቆጥቦ ማስቀመጥ በተመሳሳይ ጊዜንም ማቀድ ያስፈልጋል በመደበኛነት ከምንሰራቸው ስራዎች በተለየ ስራ ካለን መቼ እና የት መስራት እንዳለብን ማቀድ አለብን

9.3.1 በአቅም ልክ አለመመራት የሚያስከትለው ችግር

ብዙ ጊዜ ሀብት እና ንብረት ሊኖረን ይችላል ግን በእቅድ መመራት ካልቻልን ለኪሳራ ነው የምንዳረገው። እንዲሁም በወጣትነት ሰርተን ያገኘነውን ለመጦሪያችን እንዲሆነን አቅደን ማስቀመጥ አለብን

- የቁጠባ ውጤት ማለት አንድ ሰው ከሚያገኘው ገቢ ላይ እየቆጠቡ በማስቀመጥ በአጭር ጊዜና በእረጅም ጊዜ ሂደት የሚታይ ውጤት ነው።

ሀ. በአጭር ጊዜ የሚታይ የቁጠባ ውጤት

በሰዎች እለታዎ ኑሮ ውስጥ የሚከሰትን ለውጥ ይመለከታል ለምሳሌ መሰረታዊ ሂወትን ማሟላት ያልቻሉ በተለያዩ ስራዎች ተጨማሪ ነገር መግዛት ሲችሉ ምሳሌ በቀን አንዴ የሚመገቡ ከሆነ ሁለትና ሶስቴ መመገብ ቢችሉ፤ ተቀያሪ ልብስ መግዛት ቢችሉ በቆጠቡት ማር ቢችሉ ወ.ዘ.ተ

በረጅም ጊዜ የሚታዩ የቁጠባ ውጤት

ይህ የቁጠባ ዓይነት ውጤቱ የሚጣየው ከረጅም ጊዜ በኋላ ነው ሰዎች መሰረታዊ ፍላጎታቸውን ከማሟላት አልፈው ቋሚ ንብረት ለማፍራት የሚያስችል ነው። ምሳሌ ልጆችን ማስተማር ቤት የሌለው ቤት ሲኖረው አንድ ክብት የነበረው ብዙ ክብት ሲኖረው ወ.ዘ.ተ

9.3.2 በእቅድ አለመመራት የሚያስከትለው ችግር

በእቅድ አለመመራት በግላዊነት ሆነ በማህበራዊ ኑሮ ውስጥ ጉዳት ያመጣል። ዕቅድ ገንዘብ ጊዜንና ጉልበትን በአስፈላጊ ሁኔታዎችና አግባብነት ባላቸው ተግባራት ለማዋል አስተውሎ መጓዝ ነው። ይሄን አለማድረግ ጊዜን በአግባቡ እንዳንጠቀምና በሌሎ ጉዳዮች ላይ ገንዘብ እንዲባክን ያደርጋቸዋል።

ሙከራ 1

1. ቁጠባ ምንድን ነው?

2. ቁጠባ ለምን የስፈልጋል?

3. የቁጠባ ዓይነቶችን ዘርዝሩ?

4. በዓይነት የሚደረግ የቁጠባ ዓይነቶችን በምሳሌ አሳዩ

5. በዓይት የሚደረግ የቁጠባ ዓይነት እና በገንዘብ የሚደረግ የቁጠባ ዓይነት መካከል ያለውን ልዩነት በምሳሌ አሳዩ?

6. ጊዜን እንዴት መቆጠብ ይቻላል

7. የገንዘብ ቁጠባ በምናደርግበት ወቅት አስተማማኝ እንዲሆን ምን መጠቀም አለብን? ለምን

8. በሚቆጥቡ እና በማይቆጥቡ ሰዎች መካከል ያለውን የኑሮ ደረጃ እንዲሁም የአኗኗር ሁኔታ በምሳሌ አነፃጽሩ?

9. ስለ ጊዜ አጠቃቀም በሀገራችን በኢትዮጵያ ያለውን ሁኔታ በምሳሌ አሳዩ

10. ባህላዊ የቁጠባ ዘዴዎችን ዘርዝሩ?

<u>ሙከራ 2</u>

1. የቁጠባ ባህል እንዴት ይዳብራል?

2. የቁጠባ መሰረታዊ ግብን ዘርዝሩ?

3. በእቅድ መመራት ማለት ምን ማለት ነው ጠቀሜታውን ዘርዝሩ?

4. በአቅም ልክ አለመመራት የሚያስከትለውን ችግር በምሳሌ ግለጽ?

5. የአጭር ጊዜ የቁጠባ ውጤት መካከል ሁለት ምሳሌ ጥቀሱ?

   ሀ

   ለ

6. የረጅም ጊዜ የቁጠባ ውጤት መካከል ሁለት ምሳሌ ጥቀሱ?

   ሀ

   ለ

7. ዜጎች ከመሰረታዊ ፍላጎታቸው አልፈው ቋሚ ንብረት የሚያፈሩበት የቁጠባ ዓይነት የቱ ነው?

8. ልጆችን አስተምሮ ለቁም ነገር ማብቃት የትኛ የቁጠባ ዓይነት ነው?

9. በእቅድ አለመመራት የሚያስከትለውን ችግር ዘርዝሩ?

10. ተማሪዎች የቁጠባ ባህላቸውን እንዴት ማዳበር ይችላሉ በምሳሌ አሳዩ?